# የእናት እንባ።

## መታሰቢያነቱ፣ልጆቻቸው፣ያላግባብ በአጋዚ ጥይት ለተጨፈጨፉ ቤተሰቦች በሙሉ ይሁንልኝ።

አብዛኛውን ጊዜ እንባ የሚፈሰው፣
ከዐቅም በላይ ሆኖ ህዘን ሲደርስ ነው።
በደስታ ጊዜም እንባችን ቢፈስም፣
ያው ደስታ ነውና ብዙም አይጎዳንም።
እናት ኢትዮጵያም ስቃዩ በዝቶባት፣ ብዙ ታነባለች፣
ልጆቼ ምን ሆኑ ምን ቀመሱ እያለች።
ምነው አታለቅስ ምነው አታነባ ፣
ጡት ነካሽ ከሀዲ ተንጋግቶ ሲገባ።
ምነው አታለቅስ ምነው አትከፋ፣
ልጆቹዋን ያላግባብ አጋዚ ሲደፋ፣
አይዞሽ አለሁልሽ የሚላት ሲጠፋ።
ለሰሚው ግራ ነው የማይመስል ነገር፣
ወልዳ ባሳደገች እናት ስትደፈር።
ስቃይ ተደራርቦ እናት ስታለቅስ፣
ማነው የሚያስችለው እንባው የማይፈስ።
እምዬ እናታችን እስቲ ልጠይቅሽ፣
ትንሽ ይቀል እንደሁ ከባዱ ሀዘንሽ።
ሆነና ነገሩ ባጎረስኩኝ፣እጄን ተነከስኩኝ፣
ከማህፀኔ ወጥተው ስቃዬን አሳዩኝ።
ድሮም የሚጎዳው ውስጥ ዐዋቂ ነው፣
መች ተጠቅቼ ዐውቃለሁ እልፍ ባለ ሰው።
አጥብቼ አሳድጌ እንዲህ ሲያደርጉኝ፣
ሌላ ምን እላለሁ እግዜር ይፍረደኝ።
እንባዬን ያያችሁ ትሰሙኝ እንደሆን፣
ቶሎ ድረሱልኝ መሳለቂያ እንዳልሆን።
ከእንግዲህ ልጆቼ ህብረት ፍጠሩና፣
እንባዬን አብሱት አድርጋችሁ ቀና።

ይበልጣል እውነቱ።

ከጀርመን።

ሰኔ 2001
JUNE 2009-06-07